# የቱ ላይ ነው ፍቅርህ?

በጥጋቡ ዘመን አብሬህ ታድሜ
ስጠማ ጠጥቼ ስራብ ተመግቤ
ላልከዳህ ምየልህ ከአጠገብህ ላልርቅ
በሰው ፊት መሥክሬ ኪዳኔን ልጠብቅ
አሁን ትቼህ ከሔድኩ ቀራንዮ ሣለህ
ብለህ ስትጠይቀኝ የቱ ላይ ነው ፍቅርህ
ጌታዬ ጨነቀኝ ምን ልመልሥልህ

ዞትር ሥትጠራኝ ዞትር ሳንቀላፋ
ሁሌ ስትፈልገኝ ሁልጊዜ ስጠፋ
ፀፀት ከእኔ ሲርቅ ኃጢያትን ስለምዳት
ሦስት የዶሮ ጨኸት ሲያልፈኝ እንደዘበት
ብለህ ስትጠይቀኝ ምኑ ላይ ነው ፍቅርህ
ጌታዬ ጨነቀኝ ምን ልመልስልህ

ሞትህ ሞቴን ሲሽር ስቃይህ ስቃዬን
ስደትህ ስደቴን ኀዘንህ ኀዘኔን
የርህራሔህ ጥልቀት የፍቅርህ ስፋቱ
ሳይረዳኝ ሲቀር እንድሁ እንደ ከንቱ
ይህን ተገንዝበህ ብለህ ስትጠይቀኝ የቱ ላይ ነው ፍቅርህ
ጌታዬ ጨነቀኝ ምን ልመልስልህ

እንባዬ ሲታበስ ጭንቀቴ ሲፈታ
ፈጥነህ ስትደርስልኝ የጠራሁህ ለታ
ቀይ ባህር ሲከፈል ፈርኦን ሰጥሞ ሲቀር
ከበሮ እየመታሁ በደስታ ስዘምር
ቆይቼ...ቆይቼ... ሁሉን ረስቼ ...
ኃጢያት ውስጥ ገብቼ...ጣኦት አሰርቼ...
ስክድህ ስታየኝ ውሌን በጥሽብህ
ብለህ ስትጠይቀኝ የቱ ላይ ነው ፍቅርህ
ጌታዬ ጨነቀኝ ምን ልመልስልህ

ግን አምላኬ......

ደግሞ ልለምንህ የለመደ ልቤን ወዳንተ ላቅናና
ስለጴጥሮስ ብለህ የልቤን በር ቁልፍ ምታው እንደገና
በእንተ ዮሐንስ ፍቅርን አስለምደኝ
ወንድሜን ልውደደው አንተ እንደወደድከኝ
ስለዳዊት ብለህ ደጋግመህ ቀስቅሰኝ
መልስ እንዳገኝ ያኔ የቱ ላይ ነው ፍቅርህ ብለህ ስትጠይቀኝ

ወስበሀ ት ለእግዚአብሔር
ዮሴፍ አዱኛ (ታህሳስ 2001 ዓ.ም)